በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No የ.ተ.መ.2/16/46
ቀን / Date 26 ሐምሌ 2013

**ለገንዘብ ሚኒስቴር**
**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፡- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌደራልና በክልል የመንግሥት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያን ይመለከታል**

በኢትዮጵያ በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራል መ/ቤቶች እና በክልል መንግስታት አማካኝነት ተቀጥረው የሚሰሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ አከፋፈል አስመልክቶ ወጥ የሆነ እና የተጣጣመ የደመወዝ ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻል ጥናት ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ የጥናቱን ውጤት ወደ ተግባር ለማስገባት ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት የባለድርሻ አካላትን ግብዓት በመውሰድ መመሪያው ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ከሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራልና በክልል የመንግሥት መ/ቤቶች የሚቀጠሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞችን የደመወዝ አከፋፈል ስርዓትና የደመወዝ መጠንን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የተላከው 17 ገጽ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ ከነሐሴ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-
- ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ

ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
አባዘምን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

# በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ

ሐምሌ 2013
አዲስ አበባ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ያሉትን ሀገራዊ ግቦች ለማሳካት ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር በመመስረት ድጋፍ እያገኘች እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በተለያዩ መልኮች ከልማት አጋሮች ሲቀርብ የነበረው ድጋፍ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች እየተስተዋሉ ላሉት መሻሻሎች ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡ ከኢኮኖሚ ትብብሩ የሚመነጩት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በፌዴራል እና በክልል የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚተገበሩ ሲሆን በብድር ወይም በዕርዳታ መልክ የውጭ ሀብት ለማሰባሰብ እና በውስጥ አቅም ሊሸፈኑ የማይችሉትን የልማት ፍላጎቶች ለማሟላት የሚተገበሩ ናቸው፡፡

የሚቀረጹት አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ግዙፍ፣ ውስብስብ፣ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እና የተለየ ክህሎት የሚጠይቁ በመሆናቸው እንዲሁም በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ፕሮጀክቶችን የመንደፍ ወይም የማቀድ፣ የመተግበር፣ የማስተባበር፣ የመገምገም እና የተለያዩ ድጋፎችን የመስጠት የአቅም ክፍተት ያለ በመሆኑ እገዛ የሚያደርጉ ሙያተኞች እና የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኞች ቅጥር በጊዜያዊ/ኮንትራት መልክ እየተካሄደ የእነዚህን ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ለማረጋገጥ ሲሰራ እንደቆየ ይታወቃል፡፡

ሆኖም በፌዴራል እና በክልል የፕሮጀክት ፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዘው ለሚቀጠሩት የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የሚከፈለው ደመወዝ እና የሚተገበረው ጥቅማ ጥቅም እንደ ልማት አጋሮች እና ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች መለያየት ወጥነት የሌላቸውና ልዩነቱም ሰፊ በመሆኑ በጊዜያዊ/በኮንትራት ሰራተኞች ዘንድ ቅሬታን ከመፍጠራቸው ባለፈ ከፍተኛ የሰራተኞች ፍልሰት እንዲኖር በማድረግ በፕሮግራም/ፕሮጀክት አተገባበር እና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ ችግር መፍትሔ ካላገኘ ከኢኮኖሚ ትብብር የሚጠበቀው ውጤት አጥጋቢ እንዳይሆን እንደሚያደርግና በውጭ ሀብት ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሀገራዊ ግብ ስኬት ያላቸው ሚና ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይታመናል፡፡

ችግሩን ለማቃለል የተለያዩ መ/ቤቶች የራሳቸውን መፍትሔ ለማበጀት የሞከሩ ቢሆንም በተናጠል የተወሰዱት ዕርምጃዎች ዘላቂ እና ወጥ የሆነ መፍትሄ አላመጡም፡፡ ስለሆነም ይህንን ተግዳሮት ለመፍታት የተጣጣመ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ አከፋፈል አተገባበር መመሪያ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ከፌዴራል እና ከክልል የፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች አስፈጻሚ መ/ቤቶች መረጃዎችን በማሰባሰብ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ጥናት በማካሄድ ይህን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

ጥናቱ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተተገበረ ሲሆን የደመወዝ ክፍያ መጠንን ከማጣጣም ባለፈ የተለያዩ የስራ መደቦች ስያሜዎችን፣ የስራ ደረጃዎችን እና ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅትን ወጥ ለማድረግ ተችሏል። እንዲሁም ከፕሮጀክት የስራ ምድብ/ቤተሰብ አጠራር ስያሜ ሳይንሳዊ ትርጓሜ በመነሳት በተለያዩ የስራ መደብ ስያሜ ይጠሩ የነበሩ የስራ መደቦችን በማጣጣም እና አዳዲስ ስያሜ በመስጠት ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በስራ ምድብ/ቤተሰብ የመመደብ ስራ ተሰርቷል። ከዚህም በተጨማሪ እንደስራው ባህሪና ለፕሮግራም/ፕሮጀክት ትግበራ ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር በመቃኘት ቁልፍ የስራ መደቦችን ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የስራ ደረጃ እንዲኖራቸው ተደርጓል። በዚህ መመሪያ የተካተቱት ሁሉም የስራ መደቦች የዕርከን ስርዓት እንዲኖራቸውም ተደርጓል። እነዚህ ጉዳዮች በጥናቱ ውስጥ መልስ በማግኘታቸው በሀገር ደረጃ በማንኛውም የልማት አጋር ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ የስራ መደቦች ስያሜዎች፣ ደመወዝ እና ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ወጥ እንዲሆኑ በማድረግ የሰራተኞች ፍልሰትን ለመግታት ብሎም የፕሮጀክት ውጤታማነትን ለማሻሻል ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም በተደጋጋሚ ሲቀርብ የነበረውን የሰራተኞች ቅሬታ በመፍታት ፍትሐዊና ወጥ የደመወዝ ስርዓት እንዲኖር የሚያደርግ ነው።

ይህ መመሪያ በጥናቱ ትንታኔዎች እና ግኝቶች መሰረት ምክረ-ሐሳቦች ቀርበው ከባለድርሻ አካላት በተሰጡ አስተያየቶች እና ግብረ-መልስ ዳብሮ የተዘጋጀ ነው።

## የመመሪያው አስፈላጊነት

- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የተጣጣመ የደመወዝ አተገባበር በግልፅ እንዲቀመጥ በማስፈለጉ፣
- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ ለሚሰሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የተጣጣመ ደመወዝ እንዲኖር በማድረግ ፍትሃዊና ወጥ ስርዓት መገንባት በማስፈለጉ፣
- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች ከሚተገበሩ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ያሉ የስራ መደቦችን በመለየት ተመሳሳይ ባሕሪይ እያላቸው በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠሩትን መደቦች ወጥ የስራ ደረጃ እና ስያሜ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፣
- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ ለሚሰሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች ወጥነት ያለው ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት እንዲኖር በማስፈለጉ፣
- በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የተጣጣመ ደመወዝን

በተመለከተ በሁሉም የፌደራል መሥሪያ ቤቶች ወጥና ግለፅ የሆነ አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ ነው፣

## አውጭው ባለስልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር የውጭ ሀብትን የማሰባሰብና የተሰበሰበው ሀብት በታለመለት መንገድ ተግባራዊ መሆኑን እንዲከታተል በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚቀጠሩ ጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ አተገባበር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተቀጥረው ለሚሰሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የተጣጣመና ወጥነት ያለው የደመወዝ ክፍያ አተገባባር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

3.1 *"የመንግስት መሥሪያ ቤት"* ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከመንግስት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በክልል መስተዳድር ወይም በከተማ አስተዳደር ስር የሚገኝ መሥሪያ ቤት ነው፤

3.2 *"ሚኒስቴር"* ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፤

3.3 *"የልማት አጋር"* ማለት ለልማት ፕሮግራሞ/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የፋይናንስ፣ የቴክኒክ እና የዓይነት ድጋፍ በብድር ወይም በዕርዳታ መልክ በመስጠት የመንግሥትን የልማት አጀንዳ የሚደግፉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት፣ መንግሥታት፣ ቻሪቲዎችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፤

3.4 *"ፕሮግራም/ፕሮጀክት"* ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግስታት መሥሪያ ቤቶች ባለቤትነትና አስፈፃሚነት በረዥም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ የሚተገበር ፕሮግራም/ፕሮጀክት ነው፤

3.5 *"ጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኛ"* ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ 1064/2010 እንዲሁም በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ /መስከረም 2000/ በተሰጠው ትርጉም መሠረት በመንግስት መሥሪያ ቤት የዘላቂነት ባህሪ በሌለው ስራ ላይ ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡ ሆኖም፤

- ሀ) በቀን ሂሳብ እየተከፈላቸው የሚሰሩ የቀን ሰራተኞችን፤
- ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሙያ ስልጠና ወይም የስራ ልምድ ለማግኘት የሚመደቡ ተለማማጆችን፤
- ሐ) ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በገቡት ውል ዋጋ እየተከፈላቸው በራሳቸው የንግድ ስራ ወይም የሙያ ኃላፊነት የሚሰሩ ተቋራጮችን፤
- መ) ባላቸው ልዩ ዕውቀትና ችሎታ ምክንያት ከመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጋር በሚገቡት ውል መሰረት ዋጋ እየተከፈላቸው በትርፍ ጊዜያቸው የሚሰሩ ባለሙያዎችን አይጨምርም፡፡

3.6 *"የበላይ ኃላፊ"* ማለት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የሚተገበሩበት የፌደራልም ሆነ የክልል የመንግስት መሥሪያ ቤትን በበላይነት የሚመራ ኃላፊ ወይም ምክትሎቹ ናቸው፤

3.7 *"የሥራ መደብ"* ማለት በአንድ በልማት አጋር በሚደገፍ የልማት ፕሮግራም/ፕሮጀክት ተቀጥሮ በሚሰራ የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኛ ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ በቀጠረው አካል ወይም የመንግሥት መ/ቤት የተሰጡ የሥራ መዘርዝሮች፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

3.8 *"የስራ ደረጃ"* ማለት በአንድ የሥራ ምድብ/ቤተሰብ ባሉ ተመሳሳይ የስራ መደቦች ውስጥ የሚገኙ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ የሥራ መደቦች ናቸው፤

3.9 *"የስራ ምድብ/ቤተሰብ"* ማለት በስራ ባህሪያቸው ተቀራራቢ የሆኑ የስራ መደቦች በወል የሚካተቱበት ማዕቀፍ ወይም ምድብ ነው፤

3.10 *"ደመወዝ"* ማለት በአንድ የጊዜያዊ/የኮንትራት የስራ መደብ ለተቀጠረ ሰራተኛ ከመነሻ እስከ ጣሪያ ድረስ ለስራ መደቡ የተወሰነ ክፍያ ነው፤

3.11 *"ጥቅማጥቅም"* ማለት ለስራ መደቡ ከሚከፈለው ደመወዝ በተጨማሪ ሠራተኞችን ለማበረታታት በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሠጥ ማትጊያ ወይም ማበረታቻ ነው፤

3.12 *"ዝቅተኛ ተፈላጊ ዝግጅት"* ማለት የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞችን ባሉ ክፍት የስራ መደቦች ለመቅጠር፣ ለማሳደግ ወይም ለመመደብ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ነው፤

3.13 "መስፈርት" ማለት ዝቅተኛ ተፈላጊ ዝግጅትን አሟልተው በስራ መደብ ለመቀጠር በዕጩነት የቀረቡ የጊዜያዊ/የኮንትራት ስራተኞችን ችሎታና ብቃት በመመዘን ብልጫ የሚያገኙን አሸናፊዎች በክፍት የስራ ቦታው ለመመደብ የሚያገለግል ማወዳደሪያ ነው፤

3.14 "እርከን ጭማሪ" ማለት የጊዜያዊ/የኮንትራት ስራተኛው በተቀጠረበት የሥራ መደብ ሲከፈለው ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ የሚገኘው የደመወዝ ዕርከን ክፍያ ሲያገኝ ነው፤

3.15 "ድልድል" ማለት ነባር የፕሮጀክት ጊዜያዊ/የኮንትራት ሠራተኞችን በአዲስ መልክ በተዘጋጀው በዚህ መመሪያ መሰረት ለተዘጋጁ የሥራ መደቦች ተፈላጊውን የትምህርትና የሥራ ልምድ አሟልተው የተገኙ ሠራተኞችን በምደባ ወይም በውድድር መድቦ ማሠራት ነው፤

3.16 በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን ለመተግበር አዲስ ጊዜያዊ/የኮንትራት ሠራተኛ ቅጥር ሲፈጸሙ፣ ነባር የጊዜያዊ/የኮንትራት ሠራተኞችን ሲደለደል እና የደመወዝ ዕርከን ጭማሪ ሲካሄድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም፤

6.1) የመ/ቤት ወይም የመ/ቤቶች የሥራ መደቦች የደመወዝ እርከን ላይ የልማት አጋሮች ለፕሮጀክቶች ከሚመድቡት የኦፕሽን ወጪዎች ላይ በማከል ወይም top-up በማድረግ አንድ ወጥ የደመወዝ አከፋፈል ሥርዓት ተግባራዊ እንዲያደረግ በልዩ ሁኔታ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተፈቅዶ ተግባራዊ የሚያደርግ/የሚያደርጉ መ/ቤት ወይም መ/ቤቶች ላይ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

6.2) በተጨማሪም መመሪያው በልማት አጋሮች የውስጥ አሠራርና ደንብ፣ የደመወዝ ክፍያ ወሰን፣ ጥቅማጥቅም እንዲሁም የቅጥር ስርዓት በቀጥታ ተቀጥረው በመንግስት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩና ተጠሪነታቸውም ለልማት አጋሮቹ የሆኑ ተቀማጭ ሰራተኞች (Seconded Staff) ላይ ተፈፃሚ አይደረግም፡፡

6.3) ይህ መመሪያ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣው የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ (መስከረም 2000) እና የክልል መንግሥታት ያወጧቸው የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያዎች ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች ጋር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6.4) በኢፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር የልማት አጋሮች የቴክኒክ ድጋፍ ዕቅድና አጠቃቀም እንዲሁም በመንግስት መ/ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጡ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥርን አስመልክቶ የተዘጋጀው የትግባራ ማዕቀፍ (Framework for Effective Planning and

Utilization of Technical Assisstance in Ethiopian Public Instititutions) የዚህ መመሪያ አካል ሆኖ በተለይም በልዩ አማካሪ ወይም የዘርፍ-ተኮር አማካሪ የስራ ምድቦች ላይ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የስራ ምድብ ስያሜዎች መግለጫ

## 2.1 የስራ ምድብ/ቤተሰብ (Job Classification/Family)

በተለያዩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ያሉ የጊዜያዊ/የኮንትራት የስራ መደቦች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ መደቦች፣ ከድጋፍ ሰጪ እስከ ልዩ ሙያተኞች በዓይነታቸው እና ተፈላጊ ችሎታቸው የተለያዩ በመሆናቸው የስራ መደቦቹን በአምስት ዋና ዋና የስራ ምድቦች በማጠቃለል በውስጣቸው በባህሪያቸው ተቀራራቢ የሆኑ ልዩ ልዩ የስራ መደቦችን እንዲያቅፉ ተደርጓል፡፡ አምስቱ የስራ ምድቦች ልዩ አማካሪዎች (Special Advisors)፤ የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች (Sector Specific Technical Assistants)፣ የፕሮጀክት ሰራተኞች (Project Staff)፣ የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኞች (Project Management Staff)፣ እና አስዳደራዊ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (Project Support/Admin Staff) ናቸው፡፡

ልዩ አማካሪዎች እና የዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች ውስን በሆነ መጠን እና የመ/ቤቶችን ልዩ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ውስብስብ የማማከር እና ሙያዊ ዕገዛ ተግባራትን ለማከናወን በመንግስት የቴክኒክ ባለሙያዎች አቀጣጠር እና አጠቃቀም ማዕቀፍ መሰረት በልዩ ሁኔታ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የፕሮጀክት ሰራተኞች፣ የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኞች እና አስዳደራዊ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የፕሮጀክት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ፕሮጀክቶችን የማስተዳደር፣ የመተግበር፣ የመከታተል እና ድጋፍ የማድረግ አቅማቸውን ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተጠቀሱትን ፕሮጀክት-ነክ ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡

የፌደራልና የክልል የፕሮግራም/ፕሮጀክት ፈፃሚ መ/ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው አግባብ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞችን ከመቅጠራቸው በፊት የፕሮግራም/ፕሮጀክት ስራዎች በመደበኛ የመንግሥት ሰራተኞች ሊሸፈኑ ወይም መከናወን አለመቻላቸውን በማረጋገጥ ቅጥሩ ሲታመንበት ማከናወን ይገባቸዋል፡፡

የአምስቱም የስራ ምድቦች ትርጓሜ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.1.1 **ልዩ አማካሪዎች (Special Advisors)፡-** እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የመ/ቤቶችን የበላይ አመራሮችን ተቋማዊ በሆኑ የፖሊሲ እና ስትራቴጂክ-ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲያማክሩ እንዲሁም ልዩ ሙያቸውና ልምዳቸውን በመጠቀም ውስብስብ ስራዎችን እንዲያከናውኑ በልዩ ሁኔታ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምድብ የሚካተቱ የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ

ባለሙያዎች በላቀ ደረጃ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም ልምድ የሚጠይቁ የአማካሪነት ስራዎችን የሚሰሩ ናቸው፡፡

2.1.2 **ዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች** (Sector Specific Technical Assistants)፡- በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገቡት የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የሙያ አገልግሎታቸው በተቀጠሩበት ፕሮጀክት ሳይወሰን ወይም በአንድ ፕሮጀክት ሳይገታ በቀጣሪው መ/ቤት ውስጥ ባሉ የተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ ሙያዊ ግልጋሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰራተኞች የስራ ወሰን ሰፊና እንደሙያቸው ከአንድ ፕሮጀክት በላይ በሆኑ ጉዳዮች የተቋሙን ግብና ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ስራዎችን በቀጥታ እንዲያከናውኑ በልዩ ሁኔታ የሚቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡

2.1.3 **የፕሮጀክት ሰራተኞች** (Project Staff)፡- የፕሮጀክት ሰራተኞች ባላቸው የተለየ ክህሎት እና ሙያ እንደየፕሮጀክቱ ባህሪ በቀጥታ በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ውጤቶች መሳካት ቀጥተኛ ሙያዊ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በዚህ ምድብ የሚካተቱት በፕሮጀክቱ በዕቅድ የተያዙ ተግባራትን በማከናወን የፕሮጀክቱን ዓላማና ውጤቶች ለማሳካት ሙያዊ አገልግሎትን እንዲሰጡ የሚቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፡፡

2.1.4 **የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኞች** (Project Management Staff)፡- በዚህ ምድብ የሚገኙ የስራ መደቦች ላይ የሚቀጠሩ የጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞች ፕሮጀክቱን የመምራት፣ የማስተባበር ለትግበራ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣ የፕሮጀክት ትግበራን የመከታተልና ሪፖርት የማድረግ፣ የበጀትና የፋይናንስ አስተዳደር፣ ድጋፍ የማድረግ እና መሰል ስራዎችን እንዲያከናውኑ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም የፕሮጀክቱን አጠቃላይ አስዳደራዊ ስራዎችን ወይም የስራ አመራር ስራዎችን የሚያከናውኑ ሰራተኞችን ያጠቃልላል፡፡

2.1.5 **አስተዳደራዊ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች** (Project Support/Admin Staff)፡- ይህ ምድብ ለፕሮግራሙ/ለፕሮጀክቱ መሳለጥ አስተዳደራዊ የድጋፍ ስራዎችን በመከወን ድጋፍ የሚያደርጉና ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚይዝ ነው፡፡

## ክፍል ሶስት
## የደመወዝ አተገባበር አቅጣጫዎች

### 3.1 ደመወዝ

3.1.1 በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር ሲካሔድ ደመወዙ በዚህ መመሪያ ላይ ከሰንጠረዥ 1 እስከ 8 በቀረበው የደመወዝ ስኬል መሰረት ይሆናል፡፡

3.1.2 በዚህ መመሪያ የቀረበው የደመወዝ ስኬል በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌደራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች የሚከናወኑ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ ተቀጥረው እየሰሩ በሚገኙም ሆነ አዲስ በሚቀጠሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

## 3.2 አዲስ ቅጥር

3.2.1 በዚህ መመሪያ አዲስ ቅጥር ተፈጻሚ የሚሆነው ለስራ መደቡ የተወሰነውን ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉትን በማወዳደር ለሥራ መደቡ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ በመክፈል ይሆናል፡፡

3.2.2 አዲስ ቅጥር የሚፈጸምበት የስራ መደብ የስራ ደረጃ ያለው ከሆነ በዋነኛነት ፕሮጀክቱ የሚፈልገውን የስራ መጠንና ውስብስብነት ታሳቢ በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ ከተዘረዘሩት የስራ መደቦች መካከል ለስራው የሚመጥነውን በመመረጥ እና ለሥራ መደቡ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ በመክፈል ነው፡፡

3.2.3 በተ.ቁ 3.2.1 የተገለጸው እንዳለ ሆኖ አስፈላጊ ሲሆን ተወዳዳሪው ያለውን አግባብነት ያለው የስራ ልምድ፣ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች አንፃር ያለው ልዩ ዝግጅት እና በገበያው ያለው ተፈላጊነት እንዲሁም ለስራ መደቡ በዕቅድ ከተያዘው በጀት አንፃር እየታየ ደመወዙ ከስራ መደቡ ከመነሻ እስከ መጨረሻው ዕርከን ድረስ ባለው ውስጥ በድርድር ሊወሰን ይችላል፡፡

## 3.3 የነባር የጊዜያዊ ሰራተኞች ድልድል

3.3.1 ቀጣሪ መ/ቤቶች ነባር የጊዜያዊ ሰራተኞችን በዚህ መመሪያ በተቀመጡት የስራ መደቦች እንዲሁም ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት መሰረት በመደልደል አዲስ የጊዜያዊ ውል ይገባሉ፤ ድልድሉ የሚከናወነው በቀጣሪ መ/ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በውድድር ወይም በምደባ ይሆናል፤

3.3.1.1 የስራ ደረጃ ላላቸው የስራ መደቦች (ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የስራ መደቦች) ድልድሉ የሚከናወነው፡-

ሀ) መሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ ድልድል እንዲከናወንበት በሚወስነው የስራ መደብ በተቀመጠው ዝቅተኛ ተፈላጊ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት መሰረት ይሆናል፡፡

ለ) መ/ቤቱ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ካሉት የስራ መደቦች መሀከል አንድን የስራ መደብ ለድልድል ሲመርጥ በዋነኛነት ፕሮጀክቱ የሚፈልገውን የስራ መጠንና ውስብስብነት ታሳቢ በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ ከተዘረዘሩት የስራ መደቦች መካከል ለስራው የሚመጥነውን በመመረጥ ነው፡፡

3.3.1.2 ዝቅተኛውን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ የማያሟሉ፤ ነገር ግን በቂ የስራ ልምድና የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የስራ ተነሳሽነት ያላቸው ነባር ሰራተኞች ካሉ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ በሚደረግ ልዩ ውሳኔ ለአንድ ጊዜ ብቻ በያዙት የስራ መደብ ተቀራራቢ የስራ መደብ በመደልደል እንዲቆዩ ሊደረግ ይችላል።

3.3.1.3 የነባር የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች ደመወዝ አወሳሰን በሚከተለው መልኩ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

ሀ) በፊት ሲከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ደመወዝ አሁን በአዲሱ የተጣጣመ የደመወዝ ስርዓት በሚደለደሉበት የስራ መደብ ከተቀመጠው የመነሻ ደመወዝ ዝቅ ያለ እንደሆነ በአዲሱ የደመወዝ ስርዓት ለመነሻው የተቀመጠውን ወርሃዊ ደመወዝ (እርከን 0) እንዲያገኙ ይደረጋል። ለምሳሌ በአንድ የፌዴራል መ/ቤት በፕሮግራም አስተባባሪ የስራ መደብ ላይ 24,000 ብር ይከፈለው የነበረ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ መሰረት ለስራ መደቡ መነሻ የሆነውን ደመወዝ ብር 24,733 ያገኛል።

ለ) በፊት ሲከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ደመወዝ በአዲሱ የደመወዝ ስርዓት በሚመደቡበት የስራ መደቡ ከተቀመጠው የመነሻ ደመወዝ እና በመጨረሻው እርከን መካከል ከሆነ በፊት ሲያገኙት ከነበረው ወርሃዊ ደመወዝ መጠን ቀጥሎ በቅርብ በሚገኘው የአዲሱ የደመወዝ ዕርከን ላይ የተቀመጠውን ወርሃዊ ደመወዝ እንዲያገኙ ይደረጋል። ለምሳሌ በአንድ የፌዴራል መ/ቤት በፕሮግራም አስተባባሪ የስራ መደብ ላይ 28,000 ብር ይከፈለው የነበረ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ መሰረት በዚህ የስራ መደብ ሁለተኛ ዕርከን ላይ የሚገኘውን ደመወዝ ብር 29,539 ያገኛል።

ሐ) በፊት ሲከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ደመወዝ በአዲሱ የደመወዝ ስርዓት በሚመደቡበት የስራ መደቡ ከተቀመጠው የመጨረሻው እርከን ካለው ደመወዝ የሚበልጥ ከሆነ ድልደላው ከዚህ በታች በቀረበው አሰራር መሰረት ይከናወናል፡-

i. መ/ቤቶች ደመወዛቸው የሚቀንስባቸውን ሰራተኞች ስም፣ የስራ መደብ እና ደመወዝ በዝርዝር ለገንዘብ ሚኒስቴር በማቅረብ በልዩ ሁኔታ የሚደለደሉበት አግባብ ይመቻቻል፤ በዚህ አግባብ ድልድሉ እስኪከናወን ድረስ በነባሩ አሰራር በገቡት ውል መሰረት ሲያገኙ የነበረውን ደሞዝ ይዘው ይቀጥላሉ።

ii. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በልዩ ድልድል መስተናገድ የማይችሉ ሰራተኞች ካሉ በነባሩ አሰራር በገቡት የሥራ ውል መሰረት የሥራ ዘመናቸው ወይም ኮንትራታቸው እስከሚያበቃ ድረስ በያዙት የስራ መደብና ደመወዝ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ ነባሩ የኮንትራት ጊዜያቸው ሲያበቃ በተለየ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚከፈላቸውን ደመወዝ እና የስራ መደብ እንደተጠበቀ እንደመሸጋገሪያ ለመጨረሻ አንድ ዓመት ኮንትራት ሊራዘምላቸው ይችላል፡፡

## 3.4 የእርከን ጭማሪ

3.4.1 የእርከን ጭማሪ በየዓመቱ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኛው ዓመታዊ የተጠቃለለ የስራ አፈጻጸም በቅርብ የስራ ኃላፊው ተሞልቶ ከተመዘነ በኃላ ውጤቱ ሰራተኛው ለዕርከን ጭማሪ የሚያበቃው መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በየዓመቱ የሚደረገው የዕርከን ጭማሪ ከልዩ አማካሪ ምድብ ውስጥ ከሚገኙ የስራ መደቦች ውጭ ላሉ የሥራ ምድቦች በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፤

3.4.2 በልዩ አማካሪ የስራ ምድብ የሚቀጠሩ አማካሪዎች በከፍተኛ ደመወዝ በልዩ ሁኔታ የሚቀጠሩ በመሆኑ የደመወዝ ዕርከን ጭማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉት የአማካሪው የስራ አፈፃፀም ምዘና በቅርብ የስራ ኃላፊው በየዓመቱ ተሞልቶ ከተመዘነ በኃላ ለዕርከን ጭማሪ የሚያበቃው መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ በየሁለት ዓመቱ አንዴ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 3.5 ጥቅማጥቅም

3.5.1 በዚህ መመሪያ ከተገለጸው የደመወዝ ክፍያ ውጭ እንዲሁም በመመሪያው ውስጥ በግልጽ ከተቀመጠው ውጭ ለፕሮግራም/ፕሮጀክት የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች የጥቅማጥቅም ክፍያ ማድረግ አይቻልም፡፡

3.5.2 የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ (መስከረም 2000) ክፍል 6 ቁጥር 16.2 ላይ በቀረበው አኳኋን የሚታይ ሆኖ ቀጣሪው መ/ቤት ለስራው በተሳለጠ ሁኔታ መከናወን አስፈላጊ የሆኑ የስራ መሳሪያዎች እንዲያቀርብ ለቀጣሪ መ/ቤቶች ግዴታ በጣለው መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡

3.5.3 ከላይ በተ.ቁ. 3.6.2 የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ከፕሮጀክት ፕሮጀክት እንደሚለያይ ታሳቢ ሆኖ ለፕሮጀክት ስራና አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ቁሳቁሶች፣ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መገልገያዎች እና ግብዓቶች ከፕሮጀክቱ ሰራተኞች የስራ ባህሪ እና የስራ ቦታ አንፃር አስፈላጊ እና አሳማኝ ሲሆን እንደማንኛውም የፕሮጀክቱ ስራዎች በዕቅድ በፕሮጀክቱ በመያዝና ገንዘብ ሚ/ርን ጨምሮ ኃላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት ሲጸደቅ በመ/ቤቱ ከፕሮጀክቱ ወጪ በማድረግ ሊሟላ ይችላል፡፡ ይህም የጊዜያዊ/የኮንትራት

ሰራተኛው ስራውን በአግባቡ እንዲያከናውን፣ ፕሮጀክቱ በታለመለት ጊዜና በጀት ለማጠናቀቅ የፕሮጀክት አፈፃፀም ለማሳለጥ የሚያስችሉ አስፈላጊ ሁኔታዎች ከማሟላት አንጻር የሚታይ ነው።

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 4.1 መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

4.1.1 ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከፀደቀበት ከነሐሴ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡

## 4.2 የተሻሩ መመሪዎች

4.2.1 ከዚህ በፊት በልማት አጋሮች ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል የመንግስት መ/ቤቶች በሚተገበሩ ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶች የሚሰሩ የጊዜያዊ/የኮንትራት ሰራተኞች አስመልክቶ ሲሰራባቸው የነበሩ የተለያዩ የደመወዝ ስኬል እና የጥቅማጥቅም መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

## 4.3 መመሪያን ስለማሻሻል

4.3.1 ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የበላይ መሪነት በየሁለት ዓመቱ የሚከለስና የሚሻሻል ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሁለት ዓመት በፊት ወይም ዘግይቶ ሊሻሻል ይችላል።

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር ሚንስትር**

## ሰንጠረዥ 1/ የፌደራል መ/ቤቶች የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት ማናጀር (Program/Project Manager) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 38,646 | 42,400 | 46,154 | 49,908 | 53,663 | 57,417 | 61,171 | 64,925 |
| ሲኒየር የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Senior program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 30,917 | 33,920 | 36,923 | 39,927 | 42,930 | 45,933 | 48,937 | 51,940 |
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 24,733 | 27,136 | 29,539 | 31,941 | 34,344 | 36,747 | 39,149 | 41,552 |
| ረዳት የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Assis. program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 19,787 | 21,709 | 23,631 | 25,553 | 27,475 | 29,397 | 31,319 | 33,242 |
| የፋይናንስ አስተባባሪ (Finance coordinator/Specialist) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 21,000 | 23,040 | 25,080 | 27,120 | 29,160 | 31,200 | 33,240 | 35,280 |
| ሲኒየር አካውንታንት (Senior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 17,850 | 19,873 | 21,896 | 23,919 | 25,942 | 27,965 | 29,988 | |
| አካውንታንት (Accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 15,173 | 16,892 | 18,612 | 20,331 | 22,051 | 23,770 | 25,490 | |
| ጁኒር አካውንታንት (Junior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 12,897 | 14,358 | 15,820 | 17,281 | 18,743 | 20,205 | 21,666 | |
| ገንዘብ ያዥ (Cashier) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 10,962 | 12,205 | 13,447 | 14,689 | 15,932 | 17,174 | 18,416 | |
| ሲኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Senior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 21,000 | 23,380 | 25,760 | 28,140 | 30,520 | 32,900 | 35,280 | |
| የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 17,850 | 19,873 | 21,896 | 23,919 | 25,942 | 27,965 | 29,988 | |
| ጁኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Junior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 15,173 | 16,892 | 18,612 | 20,331 | 22,051 | 23,770 | 25,490 | |
| ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኛ (Senior project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 21,554 | 23,997 | 26,440 | 28,883 | 31,326 | 33,769 | 36,211 | |
| የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 18,321 | 20,398 | 22,474 | 24,550 | 26,627 | 28,703 | 30,780 | |
| መካኒክ ሹፌር/ጋራዥ ኃላፊ (Mechanic Driver/Guarage head) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 10,500 | 12,285 | 14,070 | 15,855 | 17,640 | | | |
| መካኒክ (Mechanic) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 8,750 | 10,238 | 11,725 | 13,213 | 14,700 | | | |
| ሹፌር (Driver) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,875 | 9,214 | 10,553 | 11,891 | 13,230 | | | |
| የቢሮ ረዳት/ጸሐፊ (Admin assistant/Secretary) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,656 | 8,958 | 10,259 | 11,561 | 12,863 | | | |
| ሞተረኛ (Messenger/Motorist) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 4,713 | 5,514 | 6,316 | 7,117 | 7,918 | | | |
| አጠቃላይ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ (General support staff) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 4,375 | 5,119 | 5,863 | 6,606 | 7,350 | | | |

## ሰንጠረዥ 2/ የክልል የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት ማናጀር (Program/Project Manager) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 30,917 | 33,920 | 36,923 | 39,927 | 42,930 | 45,933 | 48,937 | 51,940 |
| ሲኒየር የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Senior program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 24,733 | 27,136 | 29,539 | 31,941 | 34,344 | 36,747 | 39,149 | 41,552 |
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 19,787 | 21,709 | 23,631 | 25,553 | 27,475 | 29,397 | 31,319 | 33,242 |
| ረዳት የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Assis. program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 15,829 | 17,367 | 18,905 | 20,442 | 21,980 | 23,518 | 25,056 | 26,593 |
| የፋይናንስ አስተባባሪ (Finance coordinator/Specialist) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 19,250 | 21,120 | 22,990 | 24,860 | 26,730 | 28,600 | 30,470 | 32,340 |
| ሲኒየር አካውንታንት (Senior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 16,363 | 18,217 | 20,071 | 21,926 | 23,780 | 25,635 | 27,489 | |
| አካውንታንት (Accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 13,908 | 15,484 | 17,061 | 18,637 | 20,213 | 21,789 | 23,366 | |
| ጁኒር አካውንታንት (Junior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 11,822 | 13,162 | 14,502 | 15,841 | 17,181 | 18,521 | 19,861 | |
| ገንዘብ ያዥ (Cashier) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 10,049 | 11,187 | 12,326 | 13,465 | 14,604 | 15,743 | 16,882 | |
| ሲኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Senior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 19,250 | 21,432 | 23,613 | 25,795 | 27,977 | 30,158 | 32,340 | |
| የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 16,363 | 18,217 | 20,071 | 21,926 | 23,780 | 25,635 | 27,489 | |
| ጁኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Junior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 13,908 | 15,484 | 17,061 | 18,637 | 20,213 | 21,789 | 23,366 | |
| ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኛ (Senior project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 18,909 | 21,053 | 23,196 | 25,339 | 27,482 | 29,625 | 31,768 | |
| የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 16,073 | 17,895 | 19,716 | 21,538 | 23,359 | 25,181 | 27,003 | |
| መካኒክ ሹፌር/ጋራዥ ኃላፊ (Mechanic Driver/Guarage head) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 8,750 | 10,238 | 11,725 | 13,213 | 14,700 | | | |
| መካኒክ (Mechanic) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,875 | 9,214 | 10,553 | 11,891 | 13,230 | | | |
| ሹፌር (Driver) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,000 | 8,190 | 9,380 | 10,570 | 11,760 | | | |
| የቢሮ ረዳት/ጸሐፊ (Admin assistant/Secretary) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 6,679 | 7,814 | 8,950 | 10,085 | 11,221 | | | |
| ሞተረኛ (Messenger/Motorist) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 4,165 | 4,873 | 5,581 | 6,288 | 6,996 | | | |
| አጠቃላይ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ (General support staff) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 3,843 | 4,496 | 5,150 | 5,803 | 6,456 | | | |

## ሰንጠረዥ 3/ የዞን የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 16,625 | 18,240 | 19,855 | 21,470 | 23,085 | 24,700 | 26,315 | 27,930 |
| ሲኒየር አካውንታንት (Senior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 14,131 | 15,504 | 16,877 | 18,250 | 19,622 | 20,995 | 22,368 | 23,741 |
| አካውንታንት (Accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 12,012 | 13,373 | 14,734 | 16,095 | 17,457 | 18,818 | 20,179 | |
| ጁኒር አካውንታንት (Junior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 10,210 | 11,367 | 12,524 | 13,681 | 14,838 | 15,995 | 17,153 | |
| ገንዘብ ያዥ (Cashier) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 8,678 | 9,662 | 10,645 | 11,629 | 12,613 | 13,596 | 14,580 | |
| ሲኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Senior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 13,455 | 14,980 | 16,505 | 18,030 | 19,555 | 21,079 | 22,604 | |
| የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 11,437 | 12,733 | 14,029 | 15,325 | 16,621 | 17,917 | 19,214 | |
| ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኛ (Senior project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 14,875 | 16,561 | 18,247 | 19,933 | 21,618 | 23,304 | 24,990 | |
| የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 12,644 | 14,077 | 15,510 | 16,943 | 18,376 | 19,809 | 21,242 | |
| መካኒክ (Mechanic) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,875 | 9,214 | 10,553 | 11,891 | 13,230 | | | |
| ሹፌር (Driver) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,000 | 8,190 | 9,380 | 10,570 | 11,760 | | | |
| የቢሮ ረዳት/ጸሐፊ (Admin assistant/Secretary) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 6,125 | 7,166 | 8,208 | 9,249 | 10,290 | | | |
| አጠቃላይ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ (General support staff) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 3,843 | 4,496 | 5,150 | 5,803 | 6,456 | | | |

## ሰንጠረዥ 4/ የወረዳ የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| የፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተባባሪ (Program/project coordinator) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 16,245 | 17,823 | 19,401 | 20,979 | 22,557 | 24,135 | 25,714 | 27,292 |
| የፋይናንስ አስተባባሪ (Finance coordinator/Specialist) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 13,808 | 15,150 | 16,491 | 17,832 | 19,174 | 20,515 | 21,856 | 23,198 |
| ሲኒየር አካውንታንት (Senior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 12,427 | 13,836 | 15,244 | 16,653 | 18,061 | 19,470 | 20,878 | |
| አካውንታንት (Accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 11,185 | 12,452 | 13,720 | 14,987 | 16,255 | 17,523 | 18,790 | |
| ጁኒር አካውንታንት (Junior accountant) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 10,066 | 11,207 | 12,348 | 13,489 | 14,630 | 15,770 | 16,911 | |
| ገንዘብ ያዥ (Cashier) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 9,060 | 10,086 | 11,113 | 12,140 | 13,167 | 14,193 | 15,220 | |
| ሲኒየር የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (Senior M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 12,427 | 13,836 | 15,244 | 16,653 | 18,061 | 19,470 | 20,878 | |
| የክትትል እና ግምገማ ባለሙያ (M&E Expert) | የፕሮጀክት አስተዳደር ሰራተኛ (Project Management Staff) | 11,185 | 12,452 | 13,720 | 14,987 | 16,255 | 17,523 | 18,790 | |
| ሲኒየር የፕሮጀክት ሰራተኛ (Senior project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 12,688 | 14,125 | 15,563 | 17,001 | 18,439 | 19,877 | 21,315 | |
| የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | የፕሮጀክት ሰራተኛ (Project staff) | 11,419 | 12,713 | 14,007 | 15,301 | 16,595 | 17,889 | 19,184 | |
| መካኒክ (Mechanic) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 7,000 | 8,190 | 9,380 | 10,570 | 11,760 | | | |
| ሹፌር (Driver) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 6,344 | 7,422 | 8,501 | 9,579 | 10,658 | | | |
| የቢሮ ረዳት/ጸሐፊ (Admin assistant/Secretary) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 5,688 | 6,654 | 7,621 | 8,588 | 9,555 | | | |
| ሞተረኛ (Messenger/Motorist) | ድጋፍ ሰጪ (Admin/support staff) | 3,500 | 4,095 | 4,690 | 5,285 | 5,880 | | | |

## ሰንጠረዥ 5/ የፌደራል መ/ቤቶች የልዩ አማካሪዎች እና ዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሲኒየር ልዩ አማካሪ (Senior special advisor) | ልዩ አማካሪ (Special advisor) | 75,176 | 82,479 | 89,782 | 97,085 | 104,388 | 111,690 | 118,993 | 126,296 |
| ልዩ አማካሪ (Special advisor) | ልዩ አማካሪ (Special advisor) | 60,141 | 65,983 | 71,826 | 77,668 | 83,510 | 89,352 | 95,195 | 101,037 |
| ሲኒየር ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Senior sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 22,387 | 24,924 | 27,461 | 29,998 | 32,536 | 35,073 | 37,610 | |
| ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 19,029 | 21,185 | 23,342 | 25,499 | 27,655 | 29,812 | 31,968 | |

## ሰንጠረዥ 6/ የክልል የልዩ አማካሪዎች እና ዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሲኒየር ልዩ አማካሪ (Senior special advisor) | ልዩ አማካሪ (Special advisor) | 45,106 | 49,487 | 53,869 | 58,251 | 62,633 | 67,014 | 71,396 | 75,778 |
| ልዩ አማካሪ (Special advisor) | ልዩ አማካሪ (Special advisor) | 33,829 | 37,116 | 40,402 | 43,688 | 46,974 | 50,261 | 53,547 | 56,833 |
| ሲኒየር ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Senior sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 18,136 | 20,191 | 22,246 | 24,302 | 26,357 | 28,412 | 30,468 | |
| ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 15,415 | 17,162 | 18,909 | 20,656 | 22,403 | 24,150 | 25,898 | |

## ሰንጠረዥ 7/ የዞን የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሲኒየር ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Senior sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 14,263 | 15,879 | 17,495 | 19,112 | 20,728 | 22,345 | 23,961 | |
| ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 12,123 | 13,497 | 14,871 | 16,245 | 17,619 | 18,993 | 20,367 | |

## ሰንጠረዥ 8/ የወረዳ የዘርፍ-ተኮር የቴክኒክ ባለሙያዎች የደመወዝ ስኬል

| የስራ መደቦች ስያሜ | የስራ ምድብ/ቤተሰብ | የደመወዝ ስኬል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሲኒየር ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Senior sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 12,123 | 13,497 | 14,871 | 16,245 | 17,619 | 18,993 | 20,367 | |
| ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | ዘርፍ ተኮር የቴክኒክ ባለሙያ (Sector-specific TA) | 10,911 | 12,147 | 13,384 | 14,620 | 15,857 | 17,094 | 18,330 | |

